<u>ነገረ ድኅነት</u>

የሚያድነው እምነት እንደምን ያለ ነው?

ሐዋ 16፥30 ላይ የወህኒ ቤት ጣባቂው እነ ጳውሎስን እድን ዘንድ ምን ላድርግ ብሎ ሲጠይቃቸው " በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን" አሉት ከዚህም በመነሳት አንድ ሰው ለመዳን የግዴታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን አለብት ወደ ሚለው መደምደሚያ ያደርሰናል።
ሙስሊም ወንድም እህቶቻችን በኢሳ(በኢየሱስ) እናምናለን ይላሉ ግን ይሄ እምነት ያድናቸዋል? ብለን ስንጠይቅ መልሱ አያድናየውም ይሆናል ስለዚህ የማያድን እምነት እንዳለ በእዚ መረዳት እንችላለን።

አንድ እምነት ለድኅነት ያበቃል ወይም ያድናል ለማለት ሶስት መስፈርቶች አሉ። እነሱን ስንመለከት

1, በትክክለኛ ትምህርት ላይ የተመሰረተ(ጤናማ) መሆን አለበት

ሮሜ 10፥13-15 ስንመለከት " የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል" ይላል ሁሉ ሲል ከአይሁድ ወገንም ከአሕዛብ ወገንም ማለት ነው ከዛ ቀጥሎ "ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል" በማለት የጌታን ስም ጠርቶ ከመዳን በፊት ማመን እንደሚቀድም ያሳየናል ከማመንስ ምን ይቀድማል ካልን " ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ" የሚል መልስ እናገኛለን ስለዚህም ከማመን በፊት መስማት አለብን ሮሜ 10፥ 17 " እምነት ከመስማት ነው መስማትም የእግዚአብሔርን ቃል ነው" እንዲል ቅዱስ ጳውሎስ ይሄን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያሰማን አካል(ሰባኪ) ደግሞ ያስፈልገናል ይሄ አገልግሎት ደግሞ ለሀዋርያት ተሰጥቷቸዋል ማር 16፥15 "እንዲህም፡አላቸው፦ወደ፡ዓለም፡ኹሉ፡ኺዱ፥ወንጌልንም፡ለፍጥረት፡ኹሉ፡ስበኩ።" ይሄም እዛዉ ሮሜ 10፥15 ላይ "ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል ግን ይሄ አገልግሎት በእነርሱ አልቆመም እንዴውም በቤተክርስቲያን በኩል ቀጥሏል እንጂ ለሀዋርያት ስልጣንን ሲሰጣተቸው ማቴ 28፥18 ላይ ወደ ታች ዝቅ ስንል ጌታ "እንሆ ም፡እኔ፡እስከ፡ዓለም፡ፍጻሜ፡ድረስ፡ኹልጊዜ፡ከእናንተ፡ጋራ፡ነኝ።" ይሄም ቅዱሳን ሀዋርያት ካለፉ በኋላ ለራሱ ማስተማሩ እና ማጥመቁ በቤተክርስቲያን እስከ አሁን እንደቀጠለ ነው።
ስለዚህ ለድኅነት የሚጠቅመው እምነት የሚመጣው ለራሱ በትክክለኛው ትምህርት ላይ ስንመሰረት ነው።
ሕይወት የሚገኝበት ትምህርት እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ ይነግረናል ከዛም አልፎ ይሄን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን እንደሚመጣ ይነግረናል ስለዚህ እኛ በዚህ ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ውስጥ ካልሆንን ድኅነትን አናገኝም ማለት ነው።(ቲቶ 2፥1,2 ጢሞ 4፥3)
እንዴውም ከዛም አልፎ በኢየሱስ ትምህርት ካልሆንን እንኳን መዳንና አምላክ ለራሱ እንደሌለን መፅሐፍ ቅዱስ ይናገራል(2 ዮሐ 1፥9)።
ከምንፍቅናም መራቅ ደግሞ ለመድዳን ወሳኝ ነገር ነው(ሮሜ 16፥17,ቲቶ 3፥10,ገላ 5፥19)

2 በፍቅር የሚሰራ(ላልቶ ይነበብ) እምነት

1ኛ ቆሮ 13፥2"ትንቢትም፡ቢኖረኝ፡ምስጢርንም፡ኹሉና፡ዕውቀትን፡ኹሉ፡ባውቅ፥ተራራዎችንም፡እስካፈልስ፡ድረስ፡እምነት፡ኹሉ፡ቢኖረኝ፡ፍቅር፡ግን፡ከሌለኝ፡ከንቱ፡ነኝ።" ከዚህ በመነሳት በትክክለኛው ትምህርት ላይ የተመሰረተ እምነት ለራሱ ቢኖረን ፍቅር ግን ከሌለን ከንቱ ነን፤ እንደዚህ አይነት ተመሳሳይ ፍቺ ያለው ሌላ ጥቅስ ስንመለከት ደግሞ 1ኛ ዮሐ 2፥9"በብርሃን፡አለኹ፡የሚል፡ወንድሙንም፡የሚጠላ፡እስከ፡አኹን፡በጨለማ፡አለ።" ስለዚህ በብርሀን ሁነን ወንድማችንን ብንጠላ በጨለማ ነን ይሄ ደግሞ ፍቅር ግዴታ እንደሆነ ያሳየናል ይሄ ፍቅር ግን በአንደበት ብቻ መሆን የለበትም 1ኛ ዮሐ 3፥18። ሌላ የመጨረሻ ጥቅስ ስናይ
ገላ5፥6"በክርስቶስ፡ኢየሱስ፡ኾኖ፥በፍቅር፡የሚሠራ፡እምነት፡እንጂ፡መገረዝ፡ቢኾን፡ወይም፡አለመገረዝ፡

አይጠቅምምና።" እምነቱ ለራሱ መስራት ያለበት በፍቅር እንደሆነ ከዚህ እንረዳለን።

3 እስከ መጨረሻው የሚፀና እምነት

ማቴ10÷22"በኹሉም፡ስለ፡ስሜ፡የተጠላችኹ፡ትኾናላችኹ፤እስከ፡መጨረሻ፡የሚጸና፡ግን፡ርሱ፡ይድናል።" ስለዚህ ይሄ እምነት እስከ መጨረሻው ማፅናት አለብን በሆነ ጊዜ ላይ እምነቱን ብንተወው ድኅነትን አናገኝም ። እምነታችን እስከ መጨረሻው ከፀና ግን እንድናለን።
ሌሎች ተጨማሪ ጥቅሶች(ዕብ 3÷14,ዕብ 3÷6, ራዕ 2÷10)

የሚያድነው ስራ እንደምን ያለ ነው?

ስራ ለራሱ የሚያድንንና የማያድን ተብሎ ይከፈላል አንዳንድ ሰዎች የማያድነውን ስራ በመያዝ(በመጥቀስ) በጥቅሉ ስራ አያድንም ይላሉ ከዚህ አንፃር የሚያድነው እና የማያድነውን ስራ እናያለን።

የማያድንነው ስራ እንደምን ያለ ነው?

1በማያምኑ(በክርስቶስ እንደ አዲስ ያልተፈጠሩ) ሰዎች የሚሰራ ስራ ነው።

ይህም ማለት በአሮጌው ሰውነት ያለው ሰው ወይም ዳግም ያልተወለደ ሰው በዚህ ሁኔታ እያለ ቢሰራ አያድነውም ማለት ነው። ለምሳሌ በሐዋ ሥራ
10÷1-2"በቂሳርያም፡ኢጣሊቄ፡ለሚሉት፡ጭፍራ፡የመቶ፡አለቃ፡የኾነ፡ቆርኔሌዎስ፡የሚሉት፡አንድ፡ሰው፡ነበረ።
2፤ርሱም፡ከቤተ፡ሰዎቹ፡ኹሉ፡ጋራ፡እግዚአብሔርን፡የሚያመልክና፡የሚፈራ፡ለሕዝብም፡እጅግ፡ምጽዋት፡የሚያደርግ፡ወደ፡እግዚአብሔርም፡ኹልጊዜ፡የሚጸልይ፡ነበረ።" ግን እንደዚ መልካም ስራንም እየሰራ ቢሆንም አልዳነው ነበር ለእርሱም ቅዱስ ጳውሎስ የሚድንበትን ነገር ሂዶ መንገር ነበረበት(ምዕ 11) ስለዚህ ምንም መልካም ስራ ብንሰራ(ከማመናችን በፊት) አያድነንም።
ኤፌ 2÷8"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤" ብሎ ከተናገረ በኋላ ዝቅ ይልና "ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም" ይላል ስለዚህ ቆርኔሌዎስ ምጽዋት በመስጠቱ ነው የዳንኩት ማለት አይችልም እኛም ከማመናችን በፊት ያለው ስራችን አዳነን ማለት አንችልም። ከዛም ዝቅ ብሎ ደግሞ መልካሙን ስራ ለማድረግ በክርስቶስ ተፈጠርን ይላል መልካሙን ስራ ስላደረግን ሳይሆን ለማድረግ ተፈጠርን ከዚህ በመነሳት በእምነት ዳግመኛ ከተፈጠርን(ከተወለድን) በኋላ መልካሙን ስራ እንሰራለን ማለት ነው።
ቲቶ 3÷5"እንደ፡ምሕረቱ፡መጠን፡ለዐዲስ፡ልደት፡በሚኾነው፡መታጠብና፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡በመታደስ፡አዳነን፡እንጂ÷እኛ፡ስላደረግነው፡በጽድቅ፡ስለ፡ነበረው፡ሥራ፡አይደለም።" ስለዚህ ክርሰቶስ ያዳነን በእኛ ስራ ምክንያት ሳይሆን በምሕረቱ ባለፀጋ ከመሆኑ አንፃር ነው(ኤፌ 2÷4) ጥምቀት (ለአዲስ ልደት መታጠብ) ለራሱ የእኛ ስራ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቸርነት ነው ።

2 አይሁድ ለራሳቸው ሕጋቸው አላዳናቸውም

ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ሰው የባህርይ ውድቀት ውስጥ ስለነበር የሚፈፅመው ሕግ ሊያድነው አልቻለም።
አብርሃም አመነ እምነቱ ፅድቅ ሆኖ ተቆጠረለት ስለዚህ ሁሉም በአብርሃም ተምሳሌነት(ምሳሌ) በእምነት ወደ እግዚአብሔር ይቀርባሉ።

ሰው በእግዚአብሔር ፍት ሕግጋትን በመፈፀም ሊፀድቅ(ሊድን) አልቻለም ምክንያቱም ውድቀት ውስጥ ስለነበሩ ነው ክርስቶስ መጥቶ ይሄን ውድቀት እስኪያጠፋልን ድረስ ሕግጋት ሊፈፅሙ ለራሱ አልቻሉም።

3 ለፍቅር ውጪ የሆነ ስራ(ለታይታ የሚሰራ ስራ)

ክርስቶስ በማቴ 6÷3-5 ላይ ምፅዋት ስናወጣ በስውር እንዲሆን ይነግረናል በስውር የሚያይ አምላክ በግልጥ እንዲከፍለን ማለት ነው ነገር ግን ሰው ይየን ብለን ብንመፀውት ዋጋችንን እዛው ሰው ጋር እናገኛለን(መፅዋች ነው እንባላለን) በዚህም ምክንያት ምፅዋቱ ዋጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ አያስገኝንም ስለዚህ ስራቸን ከፍቅር የተነሳ መሆን አለበት ልክ ቅዱስ ጳውሎስ እንደነገረን(1ኛ ቆሮ 13÷3)

የሚያድነው ስራ እንዴት ያለ ነው?

የሚያድነው ስራ የተጀመረውን ድኅነት መጨረስ(መፈፀም) ነው፤ይህ ድኅነት የተጀመረው እንደ አዲስ በመፈጠር(በክርስቶስ አምኖ በመጠመቅ)ነው።

ዮሐ15÷1-2"እውነተኛ፡የወይን፡ግንድ፡እኔ፡ነኝ፤ገበሬውም፡አባቴ፡ነው።ፍሬ፡የማያፈራውን፡በእኔ፡ያለውን፡ቅርንጫፍ፡ኹሉ፡ያስወግደዋል፤ፍሬ፡የሚያፈራውንም፡ኹሉ፡አብዝቶ፡እንዲያፈራ፡ያጠራዋል።" በክርስቶስ ሆኖ ፍሬ የማያፈራ ይወገዳል ስለዚህ እኛ በክርስቶስ ብንሆንም ፍሬ ካላፈራን እንወገዳለን እንዲህ እንዳይሆን ግን መልካሙን ፍሬ(ስራ) መስራት አለብን።

አንዳንዶቹ ሰው ስራን ሰርቶ መፅደቅ ቢችል ለምን ክርስቶስ መምጣት አስፈለገው ብለው ይጠይቃሉ ለዚህ በአጭሩ መልስ የሚሆነን ክርስቶስ የመጣው ገጅምሩ መስራት እንድንችል ነው። ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት መስራት አንችልም ነበር ከመጣ ብኋላ ግን እሱ ክርስቶስ የፅድቅ ልብስ ስለሆነ ከእሱ የተነሳ መልካም ስራን መስራት እንችላለን።

በክርስቶስ አምኛለሁ እያለን ነገር ግን እንደ ብሉይ ሰዎች የፅድቅ ስራ መስራት አልችልም ካልን ሲጀመር ገና ክርስቶስን ለራሱ አለበስንውም።

ማቴ 6 ላይ እንደምናየው ለሰዎች ሀጢያታቸውን ይቅር ካልን እግዚአብሔር ደግሞ እኛን ይቅር ይለናል ይሄ ማለት ደግሞ እኛ ይቅር ካላልን እግዚአብሔር ይቅር አይልልንም ማለት ነው ለሀጢያታችን ይቅርታ ካላገኘን በሀጢያት እንኖራለን የሀጢያት ደሞዝ ደግሞ ሞት ነው ስለዚህ ከዚህ ሞት ለመገላገል ለሰዎች ሀጢያታቸውን ይቅር ማለት አለብን።

ማቴ7÷21"በሰማያት፡ያለውን፡የአባቴን፡ፈቃድ፡የሚያደርግ፡እንጂ÷ጌታ፡ሆይ÷ጌታ፡ሆይ÷የሚለኝ፡ኹሉ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡የሚገባ፡አይደለም።" ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚሉት የሚያምኑት ናቸው ግን ማመናቸው ብቻ መንግስተ ሰማያት አላስገባቸው ግን የአባቱን ፍቃድ ያደረጉት(የሰሩት) እነሱ ግን በተቃራኒው ገብተዋል ስለዚህ እምነት ካለ ስራ ከንቱ ነው ማለት እንችላለን።

ፍርድ ለራሱ ከስራ አንፃር ነው ጌታችን ማቴ 25 ላይ ለፍርድ ሲመጣ አብልታችሁኛል አጠጥታችሁኛል ብሎ ይፈርዳል ስራ ግን ለድኅነት ካላስፈለገ እንዴት ፍርድ ለራሱ በስራ ሆነ? የሚለውን ጥያቄ ያመጣብናል።